በፊንፊኔ ከተማ አስተዳደር በየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት በ2012 የትምህርት ዘመን የሁለተኛ መንፈቀ ትምህርት ለሁለተኛ ዙር የተዘጋጀ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ትምህርት ሞዴል ፈተና፡፡

መመሪያ፡-

- ***መመሪያዎቹን በጥንቃቄ አንብቡ፡፡ ስለ ፈተናው ጥያቄ ካላችሁ ፈተናው ከመጀመሩ በፊት ፈታኙን/ፈታኟን/ መጠየቅ ትችላላችሁ፡፡ ፈተናው ከተጀመረ በኋላ ምንም አይነት ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም፡፡***
- ***ይህ የአማርኛ ትምህርት ፈተና ነው፡፡ የተሰጠው ጊዜ 1 ሰአት ሲሆን ከአንድ ሰአት በላይ መስራት አይፈቀድም፡፡ ከተፈቀደው ጊዜ ቀድማቹሁ ከጨረሳቹሁ የሰራችሁትን ፈተና መከለስ ትችላላችሁ፡፡***
- ***እያንዳንዱ ጥያቄ አራት አማራጮች አሉት፡፡ ጥያቄዎቹንና ምርጫዎቹን በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ መልሳችሁን በሚሰጣችሁ የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ አመልክቱ፡፡ መልሶቻችሁን ለማመልከት ከምርጫዎቹ ስር የሚገኘውን ሳጥን አጥቁሩ/አቅልሙ/፡፡***
  - ***ለምሳሌ፡- መልሳችሁ 2ኛው ምርጫ ከሆነ ከስሩ የሚገኘውን ሳጥን በሚከተለው አኳኋን***
  - ***አጥቁሩ፡፡***

A	B	C	D
☐	■	☐	☐

- ***መልሳችሁን ለመቀየር ከፈለጋችሁ የመጀመሪያውን መልስ በደንብ አጥፉ ከዚያም ፈተናውን ለብቻችሁ መስራት ይኖርባችኋል፡፡ በማንኛውም መንገድ ለማጭበርበር ብትሞክሩ ውጤታችሁ በሙሉ ይሰረዛል፡፡***
- ***ለፈተና የተፈቀደላችሁ ሰዓት ሲያልቅ ፈታኙ/ኟ/ እንድታቆሙ ይነግሯችኋል፣ ወዲያውኑ ማቆም ይኖርባችኋል፡፡***
- ***ፈተናው እንዳለቀ መውጣት አይፈቀድም፡፡ የፈተናው ወረቀቶች እስኪሰበሰቡና ፈታኙ/ኟ/ ፈቃድ እስኪሰጧችሁ መጠበቅ አለባችሁ፡፡***

መመሪያ አንድ፡-

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ከተሰጡት አማራጮች ምረጥ/ጪ.

1. ወሮታ A. እዳ B. ኪሳራ C. ውለታ D. ብድር

2. ፍንጭ A. ምክንያት B. መንስኤ C. ማጠቃለያ D. ምልክት

3. አማተረ A. ተመለከተ B. ተራመደ C. ተከመረ D. ለካ

4 .መዘንጋት A. ማስታወስ B. መርሳት C. መረዳት D. መገረም

5. ጭቅጭቅ A. ንትርክ B. መስማማት C መዋደድ D. መራገም

መመሪያ ሁለት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ተቃራኒ ፍቺያቸውን ከተሰጡት አማራጮች ምረጥ/ጪ.

6. አዛውንት A ሽማግሌ B. ወጣት C. ጎልማሳ D. ኮረዳ

7. ጀምበር A. ቀን B. ጨረቃ C. ጸሀይ D. ኮከብ

8. ደሙፈላ A. ተገረመ B. ተናደደ C. ተበሳጨ D. ተረጋጋ

9. ማንኳሰስ A. ማሞገስ B. ማጥላላት C. መዝለፍ D. መውቀስ

10. ቀጣፊ A. ከሀዲ B. ታማኝ C. አጭበርባሪ D. ዘራፊ

መመሪያ ሶስት፡-

ከጥያቄ 11-50 የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ ምረጥ/ጪ.

11…. በትንሽ ቃላት ሰፊ መልእክት የማስተላለፍ ብቃት ያለው የስነ-ጽሁፍ ክፍል ነው፡፡

A. ልቦለድ B. ስነ-ቃል C. ግጥም D. ተውኔት

12. በሁለቱም በሬ……እያረሰ ነው፡፡ በባዶ ቦታው መግባት ያለበት ቅጥያ…….ነው

A. በሬ B. -ኣት C. -ያት D. -ዎች

13. ወንድሜ የነገረኝ ነገር በደንብ…..ገባኝም፡፡ በባዶ ቦታው መግባት ያለበት ቅጥያ…..ነው

A. ስለ B. -ኣል C. -እየ D. -ከ

14. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ቁጭት ወይም ጸጸትን የሚያመለክተው የቱ ነው?

A. ጎሽ እንኳን መጣህ B. ተው ብዬሃለሁ C. ባልመጣ ይሻል ነበር D. እንዴት ያምራል

15. እሱ ተኝቶ.....ምንም አልሰማም፡፡ በባዶ ቦታው መግባት ያለበት አያያዥ የቱነው?

A . ከዚያም B. ቢሆንም C. ነገር ግን D. ስለ ነበር

16. የሀሳብ ግንኙነት ወይም ተያያዥነት ባላቸው ሁለት ዐ.ነገሮች መካከል የሚገባ ስርአተ ነጥብ የቱ ነው? A. ፤ B. ÷ C. ፡- D. ፡፡

17. በጽሁፍ መጀመሪያና መሃል ላይ ሲመጣ የቀረ ወይም የተዘለለ ሀሳብ መኖሩን የሚያመለክት ስርአተ ነጥብ የቱነው? A. ፡፡ B. ÷ C. .... D. ፡-

18. ከቅጽል የቃል ክፍል ሊመደብ የሚችለው የቱ ነው?

A. ውሃ B. ሃገር C. ሰማይ D. ጠባብ

19. .....በዚህ ሰአት ትመጣለህ? በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ መግባት ያለበት መጠይቃዊ ቃል የቱ ነው?

A. ለምን B. የት C. መቼ D. ማን

20. .....ልትሰሪ ትመጪያለሽ? መግባት ያለበት መጠይቃዊ ቃል የቱ ነው?

A. መቼ B. ወዴት C. ምን D. ማን

21. በላ ብሎ አበላል ካለ ሰራ ብሎ.....ይላል?

A. መስራት B. ስራ C. ማሰራት D. አሰራር

22. ጨረሰ ብሎ አጨራረስ ካለ ወረደ ብሎ.....ይላል?

A. አወራረድ B. መውረድ C. ተዋረደ D. ማዋረድ

23. ሲጠብቅና ሲላላ የተለያየ ፍቺ ሊሰጥ የሚችለውቃል የቱ ነው?

A. መሪ B. መና C. ገቢ D. ውጤት

24. ከሚከተሉት አንዱ ድርብ ቃል ነው?

A. ማዝወተር B. የተጠቃለለ C.ብረ-ገብ D. መዝገብ

25. ሲጠብቅና ሲላላ የተለያየ ፍቺ ሊሰጥ የሚችለው ቃል የቱ ነው?

A. ውበት B. ገላ C. ጉም D. ሰባ

26. በሀዳሴው ግድብ የመጀመሪያ ውሃ ሙሌት ህዝቡ **ጮቤ ረገጠ** ፡፡የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ .... ነው A. ተደሰተ B. ተናደደ C. ሮጠ D. አዘነ

27. የኮሮና ባይረስ ተጠቂዎች **እያሻቀበ** መጣ፡፡ የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ .....ነው?

A. ወረደ B. ጨመረ C. ተረጋጋ D. ወጣ

28. ቴምብር የደብዳቤ .....ክፍል ነው ?

A. ውስጣዊ B. ውጫዊ C. መግቢያ D. መደምደሚያ

29. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ የቃለ አጋኖን ስርአተ ነጥብ በትክክል የያዘው ዐ.ነገር የቱ ነው?

A. እኔ እንጃ ምን! እንዳሳሰባቸው B. እኔ! እንጃ ምን እንዳሳሰባቸው

C እኔ እንጃ! ምን እንዳሳሰባቸው D. እኔ እንጃ ምን እንዳሳሰባቸው!

30. መረመረ ከሚለው ቃል ሊመሰረት የማይችለው ቃል የቱ ነው?

A. ምርምር B. አስመረመረ C. ምርመራ D. ግንባታ

31. አይኑ-ቀላ ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ፍቺው.....ነው?

A. አመመው B. ተመለከተ C. ቅናት ያዘው D. ማየት አቃተው

32. ይመጣል ብለን ስንጠብቃቸው ቀሩብን፡፡ የዚህ ዐ.ነገር ሰዋሰዋዊ ችግር.....ነው?

A. የቁጥር B. የጾታ C. የቅጥያ D. የዘርፍነት

33. ቤት ከፈተሹን በኋላ እቃቸውን ይዘውባቸው ሄዱ፡፡የዚህ ዐ.ነገር ሰዋሰዋዊ ችግር .....ነው?

A. የመደብ B. የቅጥያ አለቦታው መግባት C. የጾታ D. የቁጥር

34. ወፈ-ሰማይ ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ፍቺው

A. ወፍ ና ሰማይ B. ሰማይ ላይ ያሉ ወፎች C. የሰማይ በራሪዎች D. እጅግ ብዙ

35. የድርሰት አይነቶች.....ናቸው? A. 4 B. 3 C. 2 D. 5

36. እውነተኛ የሆነ ተጨባጭነት ያለውእና በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል ጽሁፍ.....ይባላል?

A. ልቦለድ B. ኢ-ልቦለድ C. ስነ-ጽሁፍ D. ፈጠራ

37. በገሃዱ አለም ውስጥ ሊሆኑ የሚችሉና ተአማኒነት ያላቸውን ገጠመኞች በፈጠራ መልክ ተቀናብሮ የሚቀርብ ጽሁፍ.....ይባላል?

A. ኢ-ልቦለድ B. ልቦለድ C. ድርሰት D. ስነ-ቃል

38. ስለ አንድ የተከናወነ ድርጊት በጊዜና በቦታ ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ የድርሰት አይነት ምን ይባላል? A. ገላጭ ድርሰት B. አመዛዛኝ ድርሰት
C. ተራኪ ድርሰት D. ስዕላዊ ድርሰት

39.....ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተቃራኒ ሀሳቦችን በማመዛዘን በጥሩ ሆነ በመጥፎ ጎኑ የትኛው እንደ ሚበልጥ ወይም እንደ ሚሻል የሚያሳይ የድርሰት አይነት ነው?

A. ተራኪ ድርሰት B, ገለጭ ድርሰት C. ስዕላዊ ድርሰት D. አመዛዛኝ ድርሰት

40. የተዋጠ ድምጽ ያለው ቃል የቱ ነው?

A. ባገሩ B. በአገዳ C. በአንድ D. በየአመቱ

41. ያልተዋጠ ድምጽ ያለው ቃል የቱ ነው?

A. ወዳባቱ B. እያደገ C. ለአለም D. እንዳገኘ

42. ከሚከተሉት አንዱ የተውሶ ቃል ነው?

A.ግድብ B. ዜጋ C. ሀገር D. ኢንተርኔት

43. መኪናውን **በፍጥነት** እየነዳ መጣ፡፡ የተሰመረበት ቃል

A. የስም ገላጭ B. የግስ ገላጭ C. ስም D. ግስ

44. **አስር** ደርዘን ደብተር ተገዛልኝ፡፡የተሰመረበት ቃል.....ነው?

A. ስም B. ግስ C. የስም ገላጭ D. የግስ ገላጭ

45. ምሳዬ በሚለው ቃል ውስጥ ያለው መድረሻ ቅጥያ “ ዬ” .....ያመለክታል?

A. ጾታ አመልካች B. ቁጥር አመልካች C. መደብ አመልካች D. ባለ ንብረትነት አመልካች

46. ልባችን በሚለው ቃል ውስጥ ያለው ቅጥያ .....ነው?

A. -ኣችን B. -ችን C. -ን -ልባ

47. ከሚከተሉት አንዱ በስራ ደብዳቤ ስር አይመደብም

A.ማስታወቂያ B. የሰርግ ጥሪ C. ማመልከቻ D. ማሳሰቢያ

48. ሮባ.....ኢረና ተያይዘው ሄዱ፡፡ በዚህ ዐ.ነገር መግባት ያለበት አያያዥ የቱነው?

A. ስለዚህ B. እንጂ C. ና D. እንደ

49. ኮራጁ ተማሪ በመምህሩ በፈታኙ ተያዘ፡፡በቅንፍ ውስጥ መግባት ያለበት ቃል....ነው?

A. በመምህሩ B. ኮራጁ C. ተያዘ D. በፈታኙ

50. ሃይለቃል ማለት.....ማለት ነው?

A.ዋና ዐ.ነገር B. ዝርዝር ዐ.ነገር C. አንቀጽ D. ድርሰት

መመሪያ አራት

ከጥያቄ 51-54 ድረስ በጅምር የቀረቡትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚያሟሉትን አባባሎች ምረጡ፡፡

51. አህያ ከአህያ ቢራገጥ.....

A. ምንም አይሆንም B. ጥርስ አይሳበርም C. አይኑ ይጠፋል D. ይሰባበራል

52. አፍንጫን ሲመቱት……..

A. ያማል B. ያስነጥሳል C, ይቀላል D. አይን ያለቅሳል

53. ለራሱ ሳይቀመስ የቆረሰውን ያጎርስ ለሚለው እንቆቅልሽ መልስ ሊሆን የሚችለው

A. አይን B. ምላስ C. እጅ D. አፍንጫ

54. እውነትና ንጋት እያደር……..

A. ይጠራል B. ይደፈርሳል C. ይበጠበጣል D. ይጠፋል

መመሪያ አምስት

ከጥያቄ 55-57 ያሉትን በግጥሙ መሰረት መልሱ

ደግና ክፉውን እያደባለቀ፥

መንፈሱ ለይቶ ፍርድ ካላወቀ፥

ድካሙ ከሆነ ለጌጡ ለልብሱ፥

ልፋቱ ከሆነ እስኪሞላ ከርሱ፥

ካላቀረበለት ህሊናው ወቀሳ፥

በምኑ ይበልጣል የሰው ልጅ ከእንስሳ፡፡

55. ግጥሙ……..ስንኞች አሉት? A. 5 B. 6 C. 4 D. 8

56. የመጀመሪያው ስንኝ መነሻ ሀረግ……..ነው?

A. እያደባለቀ B. ፍርድ ካላወቀ C. ደግና ክፉውን D. ህሊናው ወቀሳ

57. የስድስተኛው ስንኝ መድረሻ ሀረግ……..ነው?

A. ካላቀረበለት B. የሰው ልጅ ከእንስሳ C. በምኑ ይበልጣል D. ልፋቱ ከሆነ

መመሪያ ስድስት

ከጥያቄ 58-60 ያሉትን በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

በጥበብ እና በጥንቃቄ በወረቀት ላይ የሰፈሩ ቃላት አንባቢ ልብ ውስጥ ገብተው ያስተጋባሉ፡፡ ለደግም ሆነ ለክፉ ተግባር ይቀሰቅሳሉ፡፡ቃላት የሰውን ልጅ መብትና ግዴታ ያውጃሉ፡፡ቃላት ግፍናን ጭቆናን ያወግዛሉ፡፡ቃላት ሰላምና ህብረትን ይለፍፋሉ ለልብ ደስታን ለአእምሮ እርጋታን ይሰጣሉ፡፡ቃላት የእውቀትን ጮራ በያለበት ይፈነጥቃሉ እውነትንም ያበስራሉ፡፡በአንጻሩ ደግሞ ቃላት በሰውና በሰው በሀገርና በሀገር መካከል ጥርጣሬና ጥላቻን መፈራራትንና መራራቅን ይፈጥራሉ እውነትን በሀሰት በመሸፈን የሰዎችን መብት እንዲደፈር ያደርጋሉ፡፡ከሰማይ በታች ቃላት ሊያደርጉት የሚሳናቸው የለም ፡፡በመሆኑም ቃላትን በብዛት የሚጠቀሙባቸው ደራሲያን ጋዜጠኞች የሃይማኖትና የሀገር መሪዎች ከባድ ኃላፊነት አለባቸው የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡

58. የምንባቡ ርእስ.....ሊሆን ይችላል?

A. የቃላት ምንነት B. የቃላት ሃላፊነት C. የቃላት ኃይል D. የቃላት አፈጣጠር

59.ቃላት ሰላምና ህብረትን ይለፍፋሉ ሲል ምን ማለቱ ነው?

A.ይናገራሉ B. ያወግዛሉ C. ይደብቃሉ D. ይሰውራሉ

60. ቃላትን በብዛት ይጠቀሙባቸዋል የተባሉት የህብረተሰብ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?

A .ተማሪዎች B. መምህራን C. ደራሲያን D. ነጋዴዎች